# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ



## አንደኛ ክፍል

የ ደቡብ ብሔሮች ብረሰቦች ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ

# የእይታና የትወና ጥበባት

# የተማሪ መጽሐፍ

# አንደኛ ክፍል


አዘጋጆች፡-

ምንያህል በቀለ

ደግፌ ጌታቸው

ካሌብ ካሳ

ስዓሊ፡- ካሌብ ካሳ

ኖታ ቀራጭ፡- ምንያህል በቀለ

ኤዲተር ፡- አምዶም ገ/ዩሃንስ

ጥራት ተቆጣጣሪ፡- ተክለማሪያም ጥላሁን

ተዋበ ታደሰ

አፅዳቂ ፡- ሲዳሞ ሳልስ

ቅድስት ደፋር

ዋንቱሳ ጎንሳ

ይመኙሻል ዩሱፍ

ሃብታሙ ጳውሎስ



የ ደ ቡ ብ ብሔ ሮ ች ብረ ሰ ቦ ች ሕ ዝ ቦ ች ክ ል ል መ ን ግ ስ ት

ት ምህ ር ት ቢ ሮ

# ማውጫ


**ምዕራፍ አንድ** .......... 1

**ምልከታ** .......... 1

1.1. ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በማየት እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ድርጊቶችን መናገር .......... 2

**1.2. ከውዝዋዜ ጋር የተዛመዱ ቀላል መዝሙሮችን መስማትና መመልከት .......... 10**

1.3. ምስሎችን ፣እንቅስቃሴዎችን እና መልዕክቶችን .......... 13

1.4. ወፍራም እና ቀጭን ድምጽ መለየት .......... 21

ምዕራፍ ሁለት .......... 26

ፈጠራዊ ገለጻ .......... 26

2.1.የቤተሰብ አባላትን ተግባራት አስመስሎ .......... 27

2.2. መቸክቸክ ፣መስመር መለማመድ እና ማቅለም .......... 30

2.3.ስለ ቤተሰብ መዘመር .......... 44

2.4.ቀለል ባሉ ምቶች መወዛወዝ .......... 46

3.1.መዝሙሮች፣ቀለሞች፣ውዝዋዜዎች፣ተረቶች፣አፈ .......... 51

ታሪኮች ፣እንቆቅልሾች እና ትወናዎች .......... 51

ምዕራፍ ሦስት .......... 51

ባህሎች .......... 51

3.2. በአካባቢያችን ያሉ ቀለሞች .......... 67

ምዕራፍ አራት .......... 76

ባህላዊ ክንዋኔዎችን ማድነቅ .......... 76

4.2..አካላዊ እንቅስቃሴ .......... 93

**ምዕራፍ አምስት** .......... 95

**ጥበባዊ ትግበራ ማቅረብ** .......... 95

5.1. የህብረት ጨዋታዎች .......... 96

5.2. በህብረት መዘመር .......... 97

5.3. ስለ ተፈጥሮ ሃብት እና በዙሪያችን ስላሉ የተፈጥሮ ቀለሞች .......... 98

# ምዕራፍ አንድ
# ምልከታ

## መግቢያ

ምልከታ የተለያዩ ድርጊችን ከአካባቢያችን እንዲሁም ከተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች እንዲሁም ምስሎች በመመልከት ፣ በማዳመጥ መልዕክቶችን የምንረዳበት አንደኛው መንገድ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ከተለያዩ መልዕክት ማስተላለፊያዎች መልዕክቶችን እንረዳለን፡፡

**ተማሪዎች ይሄንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የተለያዩ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡
- ምስሎችን ተመልክታችሁ መልዕክታቸውን መረዳት ትችላላችሁ፡፡
- የድምጾችን ቅጥነት እና ውፍረት ትለያላችሁ፡፡

## 1.1. ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በማየት እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ድርጊቶችን መናገር

በቴሌቭዥን ምስሎችን ከነ እንቅስቃሴያቸው እንዲሁም ከድምጽ ጋር እንመለከታለን፡፡ እግር ኳስ ፣እሩጫ፣ሰዎች ሙዚቃ ሲጫወቱ እንዲሁም ሌሎችን ተግባራትን በቴሌቭዥን መመልከት እንችላለን፡፡

በፎቶ ፣በስዕል ደሞ ምስሎችን ብቻ ማየት እንችላለን፡፡ ፎቶ የምንለው የፎቶግራፍ መሳሪያን ተጠቅመን የምናገኘውን ምስል ሲሆን ፣ስዕል ግን በእርሳስ በማቅለሚያ እንዲሁም በተለያዩ ቁሳቁሶች ተጠቅመን በእጅ የሚሰራ ነው፡፡


**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ ፡-**የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እና መልዕክቶችን በምስል እና በድምጽ ትገነዘባላችሁ፡፡

- ተማሪዎች ከዚህ በፊት በቴሌቭዥን አይታችሁ የወደዳችሁትን ነገር ለመምህራችሁ ተናገሩ?
- ከዚህ በፊት በሌሎች መጽሀፍት ስላያችሁት ስዕል ወይም ፎቶግራፍ ተናገሩ?



ምስል 1.1 .ልጆቹ ቴሌቭዥን ሲመለከቱ

- ልጆቹ በቴሌቭዥን ምን እየተመለከቱ ነው? ያያችሁትን ተናገሩ፡፡



ምስል 1.2.

- ልጁ በቴሌቭዥን የሜዳ አህያ እየተመለከተ ነው፡፡ የሜዳ አህያ ባለ መስመር ጥቁር እና ነጭ የቆዳ ቀለም እንዳለው አያችሁ ?




ምስል 1.3.በምስሉ ልጅቷ ስታነብ እንመለከታለን



ምስል 1.4.

- እዚህ ምስል ላይ ልጆቹ ሲጫወቱ ይታያሉ እንደዚህ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ የምትጫወቱት ጨዋታ አለ? ጨዋታውስ ምን ይባላል?

# እንቅስቃሴ ያለባቸው ምስሎች



ምስል1.5. በስዕሉ ላይ ሰዎች ሲሮጡ እናያለን፡፡



ምስል 1.6 ልጁ ብስክሌት እየነዳ




ምስል 1.7

- ከላይ በምትመለከቱት ምስል ላይ ልጁ ምን እያደረገ ይታያችኋል?



ምስል 1.8

- ልጆቹ ምን ጨዋታ እየተጫወቱ ይመስላችኋል?



ምስል 1.9

- ልጁ ምን እያደረገ ነው ?



ምስል 1.10 ሰውዬው ክራር እየተጫወተ

ክራር ባህላዊ የሀገራችን የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን 6 ወይም 5 ክር አለው ። ክራርን በግርፍ ወይም በድርድር የአጨዋወት አይነት እንጫወተዋለን።

- ሰዎች ምን የሙዚቃ መሳሪያ ሲጫወቱ አይታችኋል?
- የምትወዱት የሙዚቃ መሳሪያስ ምንድን ነው ለመምህራችሁ ንገሩት

# እንቅስቃሴ የሌለባቸው ምስሎች



ምስል 1.11


ልጁ ቆሟል እየተንቀሳቀሰ አይደለም ።



ምስል 1.12

- ውሻው ምን እያደረገ ነው ? እንቅስቃሴ አለው ?


# እንቅስቃሴ ያለባቸው እና የሌለባቸው ምስሎች



ምስል 1.13



ምስል 1.14



ምስል 1.15

## 1.2. ከውዝዋዜ ጋር የተዛመዱ ቀላል መዝሙሮችን መስማትና መመልከት

ተማሪዎች በዚህ ርዕስ የተለያዩ እንቅስቃሴ ያላቸውን መዝሙሮች በቡድን እና በግል ትዘምራላችሁ፡፡

መዝሙሮቹን በምትዘምሩበት እንዲሁም በቡድን በምትጫወቱበት ጊዜ እርስ በእርስ በመረዳዳት መሆን አለበት፡፡

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ ፡-የተለያዩ መዝሙሮችን በግል እንዲሁም በቡድን መዘመር ትችላላችሁ፡፡**

- እስቲ ተማሪዎች አንድ የምታውቁትን መዝሙር ዘምሩ?

**ስምሽ ማን ነው**

ስምሽ ማን ነው ሰብለ ወንጌል
የት ትማሪያለሽ? ጫሞ ትምህርት ቤት
መቼ ትመጪያለሽ ሰኞ ማታ
ምንይዤልሽ ቸኮላታ
ማርዬ ቻቻ ማርዬ ቻቻ ኦ እንጥሼ



ምስል 1.16 ልጆ ማርዬ ቻቻ ሲጫወቱ

## መሃረቤን ያያችሁ

ልጆች መሃረቤን ያያችሁ ሲጫወቱ ፡፡



ምስል 1.17

- መሃረቤን ያያችሁ ጨዋታ የምትጫወቱት በቡድን ነው ወይስ ብቻ ለብቻ ?

## መዝሙር

መዝሙሩን ሰምታችሁ በህብረት ዘምሩ፡፡

### እንማር

እንማር እንማር

እንመራመር

ለሀገር እንድንተርፍ

እንድንከበር



ምስል 1.18 ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ

- መዝሙሩ ምን ያስተምረናል ?
- በአካባቢያችሁ የምታውቁት መዝሙር አለ? ካለ ለመምህራችሁ ዘምሩ?

## 1.3. ምስሎችን ፣እንቅስቃሴዎችን እና መልዕክቶችን

**መረዳት**

ምስሎች የተለያዩ መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ ፡-የተለያዩ ምልክት እና ምስሎችን ትለያላችሁ፡፡**

- እስቲ ተማሪዎች ከቤታችሁ ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ መንገድ ላይ ምን ምልክት አያችሁ ? ያያችሁትን ምልክት መምህራችሁ ሲጠይቃቹሁ በየተራ ንገሩት፡፡



ምስል 1.19

ይሄን ምስል ስንመለከት ቆሻሻን በአግባቡ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ብቻ መጣል እንዳለብን ይጠቁመናል፡፡



ምስል 1.20

ይሄ ምስል እጃችሁን መታጠብ ንጽህናችሁን መጠበቅ እንዳለባችሁ ያሳያል፡፡



ምስል 1.21


ምልክቱን መንገድ ላይ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ?

መንገዱ ላይ የተሰመረው መስመር ምን መልዕክት ያስተላልፋል ?



ምስል 1.22

- ይሄስ የምታዩት ምስል ምን መልዕክት ያስተላልፋል?



ምስል 1.23

- የትኛው የሴት የትኛው የወንድ ምስል እንደሆነ ለዩ፡፡ እንዴት አወቃችሁ በምን ለያችኋቸው?

ስለ ተመለከታችሁት ምስል ለአስተማሪያችሁ ተራ በተራ ንገሩት ፡፡



ምስል 1.24

- ልጆቷ ምን እያደረገች ይታያችኋል ?



ምስል 1.25

ዶክተሮች ህመምተኞችን ያክማሉ፣ይንከባከባሉ እንዲሁም ምክር ይሰጣሉ፡፡



ምስል 1.26

የህክምና ባለሙያዎች



ምስል 1.27

- ይሄስ የምን ባለሙያ ነው ?
- ሰላምታውን በማየት ሙያውን አዎቃችሁ ?




ምስል 1.28፡ በምስሉ ላይ ባለታክሲው ሰውዬ መኪናውን እየነዳ ይታያል፡፡

ባለታክሲ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ያመላልሳል፡፡

- በእናንተስ አካባቢ ሰዎች ከቦታ ቦታ ለመሄድ ምን አይነት ትራንስፖርት ነው የሚጠቀሙት?


## የተደበቁ ምስሎችን ማግኘት



ምስል 1.29

በስዕሉ ላይ የሚታየው ባቢ አሳ ለመያዝ እየሞከረ ነው፡፡ ግን አሳ ማግኘት አልቻለም፡፡አሳዎች ውሃ ውስጥ የሉም፡፡ አምስቱ አሳዎች የት ነው የሚገኙት?

## ከምስሉ ውስጥ ምን ይታያችኋል?



ምስል 1.30



ምስል 1.31

## ስንት ወፎች ይታያችኋል?

## 1.4. ወፍራም እና ቀጭን ድምጽ መለየት

ድምጾች ሲሰሙ ወፍራም እና ቀጭን ሆነው እንሰማቸዋለን፡፡ ሰዎች የተለያየ የድምጽ ቅጥነት እና ውፍረት አላቸው ፡፡አንድ አንድ ሰዎች ድምጻቸው ወፍራም ሲሆን የአንዳንዶች ደግሞ ቀጠን ይላል፡፡እንስሶችም እንዲሁም አእዋፍትም የተለያየ የድምጽ ውፍረት እና ቅጥነት አላቸው፡፡

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ** ፡-ቀጭን እና ወፍራም ድምጽ ያላቸው እንሰሳትን እና አዕዋፋትን ትለያላችሁ፡፡


- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ካሉ እንሰሳት ሲጮህ ወፍራም ድምጽ ያለው እንሰሳ ማን ነው? ለመምህራችሁ በየተራ ንገሩት ፡፡



ምስል 1.32.ልጁ በሬዲዮ ሙዚቃ እያዳመጠ ፡፡

በሬዲዮ የተለያዩ መዝሙሮች ፣ዘፈኖች እንዲሁም የሰዎችን ድምጽ ስንሰማ የድምጻቸውን ውፍረት እና ቅጥነትም መለየት እንችላለን፡፡


- በሬዲዮ ለመስማት የምትፈልጉት ምንድን ነው ?
- በሬዲዮ የምን እንሰሳ ድምጽ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ድምጹስ ወፍራም ነበር ቀጭን?



ምስሉ 1.33


ብዙ ወፎች ሲዘምሩ ድምጻቸው ቀጭን ነው፡፡

ሁልጊዜ ለሊቱ ሊነጋ ሲል የወፎችን ድምጽ እንሰማለን፡፡ ንጋት ላይ ወፎች በቀጫጭን ድምጽ ሲዘምሩ እንዲሁም የተለያየ ድምጽ ሲያወጡ መስማት የተለመደ ነው፡፡



ምስል 1.34

የዝሆን ድምጽ ደግሞ በጣም ወፍራም ነው፡፡



ምስል 1.35 . ወፍ

- ወፎች ሲዘምሩ ሰምታችኊል ?
- የወፎች ሁሉ ዝማሬያቸው አንድ አይነት ነው ወይስ ይለያያል?



ምስል 1.36

አንበሳ ሲጮህ ወፍራም ድምጽ ነው የሚያወጣው፡፡ሲጮህም ድምጹ ከእሩቅ መሰማት ይችላል፡፡

- ሌላ እናንተ የምታውቁት ወፍራም ድምጽ ያለው እንሰሳ ማን ነው ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

**በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በተንቀሳቃሽ ምስል እንዲሁም በምስል የተደገፉ ድርጊቶችንና እንቅስቃሴዎችን ተረድታችኋል፡፡**

**እንቅስቃሴዎችን የያዙ መዝሙሮችንም ዘምረናል፡፡ መዝሙርን ፣እንቅስቃሴን ፣ድርጊቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች እና ተንቀሳቃሽ ምስሎች በዚህ ምዕራፍ እየተመለከታችሁ ለመምህራችሁ ነግራችኋል፡፡የድምጽ ውፍረትእና ቅጥነትንም አውቃችኋል፡፡ ወፎች ሲዘምሩ ቀጭን ድምጽ እንዳላቸው እንደ አንበሳ እና ዝሆን ያሉ እንሰሳት ደግሞ ድምጻቸው ወፍራም እንደሆነ አውቀናል፡፡**

**መልመጃ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡**

1.ውዝዋዜ በእንቅስቃሴ የሚገለጽ ድርጊት ነው፡፡

2.ምስሎች ወይም ምልክቶች መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

3.መዝሙሮች መልዕክት የላቸውም፡፡

4.በመዝሙር መወዛወዝ ይቻላል፡፡

5. የበሬ ድምጽ ከድመት ድምጽ ይወፍራል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ፈጠራዊ ገለጻ

ስዕል፣ጽሁፍ ፣ትወና (ሚና መጫዎት)፣ሙዚቃ መጫዎት ፣ማቅለም እንዲሁም የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን መስራት ጥበባዊ ገለጻዎች ይባላሉ፡፡

ጥበባዊ ገለጻዎች ለልጆች የማወቅ ፍላጎትን በመጨመር ጥልቅ ሰሜትን በማስረጽ የፈጠራ ችሎታቸውን ያሳድጋል፡፡

## ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የተለያዩ ሚናዎችን በትወና ጥበብ ማሳየት ትችላላችሁ
- የተለያዩ መስመሮችን እና ቀላል ቅርጾችን መሰራት ትቸላላችሁ
- ስለ ቤተሰብ የሚያስተምሩ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ
- ቀላል የውዝዋዜ እንቅስቃሴዎችን ትቻላላችሁ

## 2.1.የቤተሰብ አባላትን ተግባራት አስመስሎ

### መጫወት

የቤተሰብን አባል ወይም ሌላ ተግባርን አስመስሎ መጫወት ሚና መጫወት (ትወና )ይባላል፡፡

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ ፡-** ሚና መጫወት (ትወና) ምን እንደሆነ የቤተሰቦቻችሁን ተግባራት በማስመሰል ታውቃላችሁ፡፡

- ተማሪዎቸ እስኪ የቤተሰቦቻችሁን የቤት ውስጥ ተግባራት ተናገሩ?
- እቤታችሁ ውስጥ ምግብ ማን ነው የሚያበስለው ቤቱንስ ቀለም የሚቀባው ማን ነው ?

### የቤተሰብ አባላት

እናት፣አባት፣እህት፣ወንድም፣አጎት፣አክስት፣አያት




ምስል 2.1. እናቶች ምግብ ሲያበስሉ


ቤተሰቦቻችን የተለያየ ስራ በቤት ውስጥ እንዲሁም በስራ ቦታቸው ይሰራሉ፡፡ በቤት ውስጥ ምግብ ያበስላሉ፣ቤት ያጸዳሉ ፣ልብሶች ያጥባሉ እንዲሁም የተለያየ ሰራ ይሰራሉ፡፡

ከቤተሰብ አባላት ተግባሮች ውስጥ ልጆችን መንከባከብ አንዱ ተግባር ነው፡፡

ተማሪዎች ቤተሰቦቻችሁ እናንተን እንዲሁም ወንድሞቻችሁን ፣እህቶቻችሁን እንዴት እንደሚንከባከቡ አስተማሪያችሁ በሚያሳያችሁ እና በሚነግራችሁ መሰረት አስመስላችሁ አሳዩ፡፡



ምስል 2.2.ቤተሰቦች እናት ፣አባት እና ልጆች



ምስል 2.3.አባት በእርሻ ስራ ላይ ።



ምስል 2.4.እናት ልጇን ጡት እያጠባች

አባት እርሻ ያርሳል፣ልጆቹን ይንከባከባል፡፡

እናት ጥጥ ትፈትላለች፣ምግብ ታበስላለች፣ልጆቿን ትንከባከባለች፡፡


ቤተሰብ ውስጥ የልጆች ተግባር ትምህርት ይማራሉ፣ ቤተሰቦቻቸውን በቀላል ስራዎች ላይ ማገዝ፡፡

## 2.2. መቸክቸክ ፣መስመር መለማመድ እና ማቅለም

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ :-** እጃችሁን ለማፍታታት ችክቸካዎችን ትለማመዳላችሁ እንዲሁም የተለያዩ መስመሮችን መስራት ትችላላችሁ፡፡ የቅርጾችን ውስጠኛ ክፍል ማቅለም ትችላላችሁ፡፡

- ተማሪዎች እስኪ ወረቀት ላይ የፈለጋችሁትም ምስል ስሩ ?

**በቀለም እርሳሶች የተቸከቸኩ ምስሎች**



ምስል 2.5

## 2.2.1.ሶስት አይነት ችክቸካዎችን መለማመድ


መቸክቸክ ማለት በእርሳስ እንዲሁም በሌላ መጻፊያ እጅን ወደ ፈለጉት አቅጣጫ በማስኬድ የተለያዩ መስመር መሰል እና እጥፋቶች መስራት ማለት ነው፡፡

ልጆች መቸክቸክ እጃችሁ በደንብ ስዕል ለመሳል ፣ለመጻፍ እንዲፍታታ ያደርግላችኋል፡፡

- ችክቸካ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመምህራችሁ ተናገሩ?


**ከዚህ በታች ያሉትን አይነት ችክቸካዎች በደብተሮቻችሁ ላይ ተለማመዱ**

I. ወደ ጎን (አግድሞሽ )መቸክቸክ




____________________________

II. ወደ ታች የሚወርድ መቸክቸክ



____________________________

## III. ክብ መስመሮችን በሚሰራ መልኩ መቸክቸክ



ልጆች ሶስቱንም ችክቸካ ለይታችሁ ከተለማመዳችሁ በኋላ ሶስቱንም በአንድ ላይ በማድረግ ችክቸካውን ተለማመዱ፡፡

### 2.2.2.. የመስመር አይነቶች

**ቋሚ መስመር**


ከላይ ወደ ታች የሚወርድ ቀጥ ያለ መስመር

**አግድም መስመር**

ከመሬት ጋር ትይዩ የሚሄድ መስመር (ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀይ ወደ ግራ የሚሰመር ቀጥ ያለ መስመር)


**ሰያፍ መስመር**

ቀጥ ያለ ሆኖ በግማሽ የወደቀ መስመር




**ታጣፊ ወይም ቆልማማ መስመር**

የክብ መስመር ተቆርጦ የወጣ መሳይ መስመር




**ዚግዛግ መስመር**

የሰያፍ መስመሮች ስሪት ሲሆን የተቆራረጠ ውጣ ውረድን የሚያሳይ መስመር ነው




**ሞገዳማ መስመር**

**ቆልመም ባለ መታጠፊያ ከፍ ዝቅ የሚል መስመር**




**ሽክርክር መስመር**

ደጋግሞ የሚዞር መስመር ነው፡፡



**ከዚህ በታች ያሉትን መስመሮች ተለማመዱ**


**ያልደመቁትን መስመሮች ማድመቅ፡፡ይሄንን ልምምድ በሌላ መለማመጃ ደብተራችሁ ላይ ተለማመዱ፡፡**




**መስመሮችን በመጠቀም ቅርጽ መስራት**



መስመሮችን በተለያየ ነገር ላይ እንመለከታቸዋለን ፡፡አንድ ሰው ሲቆም ቀጥ ያለ መስመር ይሰራል፡፡




ምስል 2.7



ምስል 2.8


ሰው ሲተኛ ደሞ አግድም መስመር ይሰራል፡፡

- ከታች የምትመለከቷት ልጅ ምን አይነት መስመር ነው የሰራችው?



ምስል 2.9

## በችክቸካ እና በመስመር ስዕል መለማመድ




ምስል 2.6.በችክቸካ የተሳለ ስዕል

## 2.2.3.ቅርጾች

ልታውቋቸው የሚገቡ ቅርጾች፡፡


### እኩል አራት ማዕዘን ቅርጽ

በአራቱም ጎን ያሉ መስመሮች እኩል ልኬት ይኖራቸዋል




### አራት ጎን ያለው ቅርጽ

አራት ጠርዝ ያለው ቅርጽ ነው፡፡ ቋሚ እና አግዳሚው መስመር እኩል ልኬታ የላቸውም፡፡




## ክብ ቅርጽ




## ሞላላ ቅርጽ

እንደ እንቁላል አይነት ሞለል ያለ ክብ ቅርጽ መሳይ ነው።




## ሶስት ጎን ያለው ቅርጽ

ሶስት መዐዘን ቅርጽ ሶስት ጠርዞች ያሉት መስመር ነው።




## አምስት መዐዘን የያዘ ቅርጽ

አምስት ጠርዞች ያሉት ቅርጽ ነው፡፡




## የኮከብ ቅርጽ


የከዋክብት ቅርጽ በጨለማ ከሰማይ ላይ የምናያቸው ኮከቦች አይነት ቅርጽ ነው፡፡



የምናያቸው ነገሮች ብዙዎቹ የራሳቸው ቅርጽ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ሳጥን አራት ማዕዘን አለው፡፡



ምስል .2.10



ምስል.2.11

እንቁላል ደሞ ሞላላ ቅርጽ አለው፡፡



ምስል 2.12

ኳስ ክብ ቅርጽ አለው፡፡

ከኳስ ሌላ ክብ ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች ለመምህራችሁ ተናገሩ?

እንዲሁም ከሳጥን ሌላ አራት መዕዘን ያላቸውን ነገሮች ተናገሩ?

## ነጥቦችን በመጠቀም ቅርጾችን እና መስመሮችን መስራት


### አግድም ቀጥ ያለ መስመር አሰራር

ሁለት ነጥቦችን ማስቀመጥ፡፡ሁለቱ ነጥቦችን በመስመር ማገናኘት




### አራት መዐዘን አሰራር

አራት ነጥቦችን ማስቀመጥ ፡፡ነጥቦችቹን ቀጥ ባለ መስመር ማገናኘት፡፡



## 2.2.4. ቅርጾችን ማቅለም

ተማሪዎች ከታች እንደምትመለከቷቸው አይነት ቅርጾችን መሃለኛውን ክፍል ማቅለም ትለማመዳላችሁ፡፡በእርሳስ ፣በእስክርቢቶ ወይም ቀለም ባላቸው መጻፊያዎች ማቅለም ትችላላችሁ፡፡ ተማሪዎች ማቅለም ያለባችሁ መጽሃፋችሁ ላይ ሳይሆን ሌላ መለማመጃ ደብተራችሁ ላይ ነው፡፡




## 2.3.ስለ ቤተሰብ መዘመር

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ ፡- የተለያዩ ስለ ቤተሰብ የሚናገሩ መዝሙሮችን መዘመር ትችላላችሁ፡፡**

- ተማሪዎቸ እስኪ የምታውቁትን መዝሙር ለመምህራችሁ ተናገሩ?

ስለ አባት ፣እናት፣ እህት፣ ወንድም የተዘመሩ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡



ምስል 2.13

**እወዳችኋለሁ**

አባ.......ቴ

እና......ቴ

ወንድሜ እህቴ

እውዳችኋለሁ ከራሴ አብልጩ

- ከላይ ያለው መዝሙር ስለ ምንድን ነው የሚነግረን?

## ወንድሜ ያዕቆብ

ወንድሜ ያእቆብ
ወንድሜ ያዕቆብ
ተኝተሃል ወይ
አትነሳም ወይ
ደውል ተደወለ
ደውል ተደወለ
ተነሳ ተነሳ
እህቴ የሺ
እህቴ የሺ
ተኝተሻል ወይ
አትነሺም ወይ
ደውል ተደወለ
ደውል ተደወለ
ተነሺ ተነሺ

ስለወንድሞቻችን ስለ እህቶቻችን የሚናገር መዝሙር በመቀጠል እንዘምራለን፡፡ መምህራችሁ መዝሙሩን ከዘመሩላችሁ በኋላ እናንተ ተከትላችሁ ዘምሩ፡፡

**እንዴት ነሽ**

.

.

**የወንድሜ የእህቴ ጓደኛ**

**እንዴት ነሽ እንዴት ነሽ ንገሪኛ**

እናቶች ልጆቻቸውን ሲያስተኙ አይታችኋል ዜማውንስ ታውቁታላችሁ ?

**እሹሩሩሩ**

እሹሩሩሩ እሹሩሩሩ

የማሙዬ እናት ቆሎ ነይለት

ወተቱን በጉያ


ዳቦውን ባህያ

ይዘሽለት ነይ እሹሩሩሩ

## 2.4.ቀለል ባሉ ምቶች መወዛወዝ

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ ፡- ቀለል ባሉ ምቶች መንቀሳቀስ እና የተለያዩ መዝሙሮችን በውዝዋዜ መግለጽ ትችላላችሁ፡፡**

- መምህራችሁ በሚሰጣችሁ ቀላል ምቶች ከመዝሙሮች ጋር ተወዛወዙ፡፡



ምስል 2.14

እግሮቻችን እና እጆቻችን ከጓደኞቻችን እርስ በእርስ በማነካካት የተለያየ ጨዋታ መጫወት እንችላለን፡፡ እግሮቻችንን እንዲሁም እጆቻችንን በማጋጨት ከመዝሙር ጋር የምንጫወታቸው ጨዋታዎች አሉ፡፡

**በሁለቱ እጆቼ ቸብ ቸብ ቸብ**
**በእግሮቼ ጣቶች ትም ትም ትም**
**በሁለቱ ጣቶቼ ቀጭ ቀጭ ቀጭ**
**በሁለቱ እግሮቼ  እንጣጥ እንጣጥ እንጣጥ**
**እላለሁ እጫወታለሁ**
**እላለሁ እጫወታለሁ**

እስኪ እናንተ የምታውቁት ጨዋታ ምንድን ነው?



ምስል 2.15

## ሸረሪቷ ቀስ በቀስ

ሸረሪት ቀስ ብላ በድሯ ላይ ወደ ላይ ስትወጣ በእጃችሁ እንቅስቃሴ እያሳያችሁ የምትዘምሩት መዝሙር፡፡



ምስል 2.16

ሸረሪቷ….ቀስ በቀስ…

ቀስ በቀስ …….

ወደ ላይ ወጣች

ንፋሱ መጥቶ……..

ወደ ቀኝ ወደ ግራ አደረጋት

**ድንብሽ ለድንብሽ**

ድንብሽ ለድንብሽ ድንብሽ ኖራ

ኖራ መስኮራ መስኮርኮርኪ

ኮርኪ ሰላሌ ስላሌንቦ

ሌንቦ ክፍሌ ሌንቦ

ክፍሌ ላንቃ



ምስል. 2.17.ልጆች ድንቡሽ ለድንቡሽ ሲጫወቱ




**መልመጃዎች**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1.  ይህ መስመር ምን መስመር ይባላል፡፡

ሀ. አግድም ለ. ቀጥታ ሐ. ዚግዛግ



2. ከሚከተሉት ቅርጾች ውስጥ ሞላላ ቅርጽ የትኛው ነው፡፡

ሀ.  ለ.  ሐ. 

3. ህጻን ልጅ ለማስተኛት የማባበያ መዝሙር የትኛው ነው?

ሀ. እሹሩሩሩ ለ.ወንድሜ ያዕቆብ ሐ.እንማር

4. ከነዚህ ቅርጾች ውስጥ ውስጡ የተቀባው የትኛው ነው

ሀ.  ለ.  ሐ. 

# ምዕራፍ ሦስት
# ባህሎች

## አካባቢ እና ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጥበቦች

ባህል ማለት የህዝቦች ልማድ፣ የአመጋገብ፣የአለባበስ፣ የሙዚቃ፣ የውዝዋዜ ሰርዓት ነው፡፡ በሀገራችንም የተለያዩ ውብ ባህሎች ይገኛሉ፡፡ የተለያዩ ባህሎችን በተረቶች፣ በአልባሳቶች፣ በውዝዋዜዎች ፣በእንቆቅልሾች መማር እንችላለን፡፡

## ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የተለያዩ ተረቶችን ፣እንቆቀልሾችን እንዲሁም አፈታሪኮችን ታውቃላችሁ
- የተለያዩ የባህል ውዝዋዜዎችን መለየት ትችላላችሁ
- በአካባቢያችሁ ያሉ ቀለማትን መለየት ትችላላችሁ

## 3.1.መዝሙሮች፣ቀለሞች፣ውዝዋዜዎች፣ተረቶች፣አፈ ታሪኮች ፣እንቆቅልሾች እና ትወናዎች

### 3.1.1.ተረቶች

ተረት ማለት ስለ ተለያዩ ነገሮች የሚነግረን የሚያስተምረን ታሪክ ማለት ነው፡፡

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ ፡-የተለያዩ ተረቶችን ታውቃላችሁ፡፡**

- እስቲ ተማሪዎች አንድ የምታውቁትን ተረት ለመምህራችሁ ንገሩት?

## ተረት- 1

## ቀበሮ እና አውራ ዶሮ

አንድ ቀን አንድ ቀበሮ ምግብ ፍለጋ ወደ ሰዎች መኖሪያ መንደር መጣ፡፡በመንደሩ አንድ አውራ ዶሮ አንድ ድንጋይ ላይ ቆሞ ኩሉሉ …….እያለ ሲጮህ ቀበሮው ሰማና ወደ አውራ ዶሮ ቀረብ ብሎ

“ሰላም ላንተ ይሁን ወንድሜ አውራ ዶሮ እንደምን ዋልክ” አለው::

አውራ ዶሮውም“ የዶሮ አምላክ ይመስገንና ሰላም ነኝ” ሲል መለሰ፡፡ቀበሮም ቀጠል አድርጎ፣

“ወንድሙ አውራ ዶሮ ከእሩቅ ሆኜ ድምጽህን ስሰማ ደስ የሚል መሆኑን ተረዳሁ፡፡በእርግጥም ድምጽህ በጣም ደስ ይላል፡፡ ወደዚህም የመጣሁት ቀረብ ብዬ ብሰማው እንዴት ደስ እንደሚል ለማረጋገጥ ነውና ፣እስቲ እባክህ አንዴ ቀረብ በለኝና አሰማኝ” ሲል ለመነው::



ምስል. 3.1

አውራ ዶሮውም በቀበሮው ሙገሳ እጅግ በጣም ተደሰተ ወዲያውም ወደ ቀበሮው ቀረብ በማለት ጎንበስ ቀና አለና አይኑን ጨፍኖ ኩኩሉሉ…ኡኡ….ብሎ ሳይጨርስ ቀበሮውም ዘሎ የዶሮውን ክንፍ ጭምድዶ ይዞ ወደ ዋሻው ይዞት መሮጥ ጀመረ፡፡


እረኞችም ቀበሮ ዶሮውን ይዞት ሲሮጥ አይተው ኖሮ ከኋላ እየተከተሉ ያሳድዱት ጀመር፡፡በዚህ ጊዜ አውራ ዶሮ አንድ መላ መጣለት፡፡

"ይህውልህ ወዳጄ ቀበሮ እረኞች ዶሯችንን ወሰደ እያሉ እየሮጡ ነው ፡፡ተከታትለው መጥተው እንዳይደበድቡህ ፡፡ የእናንተ ዶሮ አይደለም በላቸው" ሲል ዶሮው ቀበሮውን መከረው፡፡

ቀበሮውም እውነት መስሎት ወደ እረኞቹ ዞሮ ፤

“እናንተ እረኞች ዶሮው የእናንተ አይደለም የኔ ነው” ሲል ። አውራ ዶሮውም ከቀበሮው አፍ አፈትልኮ በመሮጥ አንድ ዛፍ ላይ ወጥቶ ቁጭ አለ። ከዛም ዶሮው ቀበሮውን ቁልቁል እየተመለከተ

“ይሄውልህ ወዳጄ ቀበሮ በአለም ላይ አንተ ብቻ ብልጥ የሆንክ እንዳይመስልህ። በብልጠት ማታለል የጥሩ ስነ ምግባር ድርጊት አይደለም እሺ።” ሲል ተናግሮ ከዛፉ ላይ ዘሎ በመውረድ አመለጠ።



ምስል .3.2

- አሁን ካነበባችሁት ተረት ምን ተማራችሁ?
- በተረት ውስጥ ያሉት እነማን ናቸው ?


## ተረት -2

## አንበሳ እና አይጥ

አንድ ወቅት የእንስሶች ንጉስ የነበረ አንድ አንበሳ በጫካ ውስጥ ይኖር ነበር፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ይህ አንበሳ ምግቡን ፍለጋ ከጫካ ውስጥ ሲዘዋወር አንዲት አይጥ አገኘ፡፡ አይጧንም አግኝቶ ሊበላት ሲል “አያ አንበሳ እባክህ አትብላኝ” አለችው፡፡አያ አንበሳም “ዛሬ እርቦኛል አንቺን ካልበላሁ ታዲያ ምን ልብላ?” ሲል ተናገረ፡፡


አይጧም “የዛሬን ማረኝ እንጂ አንድ ቀን ውለታህን እመልሳለሁ” አለችው፡፡ አንቺ በአካልሽ ትንሽ ነሽ እንዴት ለእኔ ውለታ ትመልሻለሽ አላት፡፡ የዛሬን ማረኝ እንጂ አንድ ቀን ውለታህን እመልሳለሁ አለች፡፡



ምስል .3.3


አንበሳው እየሳቀ “በይ ለዛሬ ሂጂ” ብሎ አዘነላትና ለቀቃት፡፡አይጧም እየሮጠች ከፊቱ ሄደች፡፡ አንበሳውም የወደቀ ስጋ አገኘና በልቶ ረሃቡን አስታገሰ፡፡

ከጥቂት ጊዚያት በኋላ አንበሳው የሚበላ ስጋ ፍለጋ በጫካው ውስጥ ሲዘዋወር ድንገት አዳኞች የአዘጋጁት የገመድ ወጥመድ ውስጥ ገባ ፡፡



ምስል .3.4

አንበሳው ቢታገል ቢታገል ገመዱን መፍታት አልቻለም፡፡ ያን እለት አይጥ በአጋጣሚ መንገድ ስታልፍ አንበሳ ታስሮ አየች፡፡ ወደ አንበሳውም በመቅረብ “እያ አንበሳ አሁን ገመዱን ቆርጬ ከገባህበት ገመድ አስወጣሃለሁ፡፡”



ምስል.3.5

የአይጥ ጥርስ ጠንካራ እና ብዙ ነገር መቁረጥ የሚችል ስለሆነ አይጧ ገመዱን በፍጥነት ቆርጣ ጣለችው፡፡ አንበሳውም ነጻ ወጣ ፡፡ አንበሳውም ውለታህን እመልሳለሁ ያለችውን አስታውሶ በጣም ተገረመ፡፡አይጧን አመስግኗት በሰላም ወደ ቤቱ ሄደ፡፡

ልጆች ከተረቱ መልካም ነገር ማድረግ ቆይቶ የሚጠቅመው ለራስ እንደሆነ ተማራችሁ?

## እንቆቅልሽ ጨዋታ

ልጆች እንቆቅልሽ ጨዋታ በቡድን ሆናችሁ የምትጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡

በጨዋታው ጠያቂ እና መላሽ ይኖራል፡፡ጠያቂ እንቆቅልሽ ብሎ ይጀምራል፡፡

መላሽ ምን አውቅልህ ብሎ ይመልሳል፡፡ ከዛ ጠያቂው ጥያቄውን ይጠይቃል፡፡

## እንቆቅልሽ

እንቆቅልሽ በጥያቄና መልስ ድብቅ ሃሳቦችን በጨዋታ መልክ የምንማርበት ዜዴ ነው፡፡

እንቆቅልሽ ጨዋታ የሚጫወቱት  ጠያቂ እና ጥያቄውን የሚመልስ ሰው በመሆን ነው፡፡

- መጀመሪያ ጠያቂው ምን ብሎ ይጀምራል ? ከዛስ መላሽ ምን ይላል የሚለውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## 1.የእንቆቅልሽ ጨዋታዎች

1.ትልቁ አዞ ተጠማዞ

2.አራት እግር አለው ወንዝ የማይሻገር

3.ከቁርስ በፊት የማይበላ

4.ጸጉሯን አበጥራ ገበያ የምትወጣ

5.ከመብላታችን በፊት የምንሰብረው

6.እናትየው ጥቁር ለጆቿ ነጫጭ

7.ገላዬ ብርቱካናማ ኮፍያዬ አረንጓዴ እኔ ማን ነኝ

8.ወጣት ሳለሁ እረዝማለሁ ሳረጅ አጥራለሁ እኔ ማን ነኝ

9.በራሴ አፍ የለኝም ግን ሰዎች የተናገሩትን እደግማለሁ

10.ንጹህ ሲሆን የሚጠቁር ሲቆሽሽ ነጭ የሚሆን

11.ላዩ በድን ታቹ በድን መሃሉ ነፍስ አድን

12.ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ

## 3.1.2. ውዝዋዜዎች

በሃገራችን የተለያዩ አይነት ውዝዋዜዎች አሉ፡፡ወዝዋዜዎች ስለ ሰዎች ባህል  የምናውቅበት አንዱ ዘዴ ነው፡፡በሃገራችን የተለያዩ ባህሎች አሉ እነዚህም ባህሎች የተለያየ የሙዚቃ ምት እና የአጨፋፈር ስርዓት አላቸው፡፡

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ** ፡-የተለያዩ ውዝዋዜዎችን ትመለከታላችሁ፡፡እንዲሁም ውዝዋዜዎቹን  በጥቂቱ ትወዛወዛላችሁ፡፡

- እስቲ ምታውቁትን የባህል ውዝዋዜ አሳዩ ?
- በአካባቢያችሁ ያለው ምን አይነት ውዝዋዜ ነው?

በቴሌቭዥንስ ምን አይነት ጭፈራ ወይም ውዝዋዜ ተመልክታችኋል?



ምስል 3.6

በሃገራችን ከሚገኙ ውዝዋዜዎች ውስጥ ጥቂቱን ከታች በምስሉ ተመልከቱ። ምስሉ ላይ ከውዝዋዜው በተጨማሪ የባህሉን አለባበስም ይዟል።እንደ ባህሉ ጭፈራ የአለባበስ ስርዓቱም እንደ አካባቢው የተለየ ነው ።



ምስል 3.7 የጋሞ ማህበረሰብ ባህላዊ ጭፈራ



ምስል 3.8 የኛንጋቶም ማህበረሰብ ባህላዊ ጭፈራ

ተማሪዎች በዚህ ጭፈራ ላይ አለባበሳቸውን አያችሁ?



ምስል 3.9. የኮንሶ ማህበረሰብ ጭፈራ



ምስል 3.10. የደራሼ ማህበረሰብ ጭፈራ

እንደዚህ አይነትስ ጭፈራ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ?



ምስል 3.11 የጉራጌ ማህበረሰብ ባህላዊ ጭፈራ

- ይሄስ ጭፈራ በአካባቢያችሁ ካለው ጭፈራ ጋር ይመሳሰላል ወይስ ይለያል?አለባበሳቸውንስ አያችሁ ?



ምስል 3.12 የሱማሌ ማህበረሰብ ጭፈራ



ምስል .3.13 ኦሮሞ ማህበረሰብ ጭፈራ



ምስል 3.14 የአማራ ማህበረሰብ ጭፈራ

ተማሪዎች መምህራችሁ በሚያሳያችሁ መሰረት የተለያዩ ጭፈራዎችን በቡድን እንዲሁም በግል ተለማመዱ ::

## 3.1.3.መዝሙሮች

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ ፡-የተለያዩ መዝሙሮችን መዘመር ትችላላችሁ፡፡**

እስቲ ምታውቁትን መዝሙር ዘምራችሁ ለመምህራችሁ አሰሙ ?

የሚከተለውን መዝሙር መምህራችሁ በሚሰጣችሁ ዜማ መሰረት ዘምሩት ፡፡

### ዝናብ ሂድልኝ

ዝናብ ሂድልኝ ነገ ተመለስልኝ
ዝናብ ሂድልኝ ዛሬ ጨዋታ አለብኝ



ምስል .3.15

ቡደን ጨዋታ ከመዝሙር ጋር ፡፡

## ልጅ ለመፈለግ መጥተናል ዛሬ በማለዳ

ልጅ ለመፈለግ መጥተናል ዛሬ በማለዳ
ማንን ትፈልጋላችሁ ዛሬ በማለዳ
ሚሚን እንፈልጋታለን ዛሬ በማለዳ
እሷን መጥቶ የሚወስዳት ማን ጎበዝ አላችሁ
እሷን መጥቶ የሚወስዳት አቡሻ አለና
የኛ ልጅ በርቺ በርቺ እንዳትረቺ
የኛ ልጅ በርታ በርታ እንዳትረታ



ምስል 3.16

## 3.2. በአካባቢያችን ያሉ ቀለሞች


አካባቢያች በተለያዩ ቀለሞች የደመቀ ነው፡፡ልብሳችን ፣የቤት ግድግዳችን ፣የእንሰሳ ቆዳ ቀለሞች እና ሌሎችም ነገሮች ሁሉ የራሳቸው አይነትቀለም አላቸው፡፡

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ** ፡- የተለያዩ ቀለሞችን መለየት ትችላላችሁ፡፡እንዲሁም የባንዲራ ቀለማትን የልብስ ቀለማትን በስዕል ላይ ማቅለም ትችላላችሁ፡፡

ተማሪዎች እስቲ አጠገባችሁ የተቀመጠውን የጓደኛችሁን የልብስ ቀለም ተናገሩ ?




ቀይቀለም




ብርቱካናማ ቀለም



ቡኒቀለም



ሰማያዊ ቀለም



ቢጫ ቀለም

ጎጆ



ምስል 3.17.ከውጪ ግድግዳው የተቀባ

ግድግዳው ላይ ምን አይነት ቀለም አያችሁ በሩ ላይስ ምን አይነት ቀለም ይታያችኋል



ምስል .3.18

ከላይ ያለውን ምስል ግድግዳውን በቢጫ በሩን በቀይ ጣራውን በጥቁር ቀለም አቅልሙ

## የአልባሳት ቀለም

ሰማያዊ ኮት



ቀይ ቁምጣ



አረንጓዴ ካኒቴራ



ቢጫ ቀሚስ



ምስል .3.19

- ልጆች የለበሳችሁት ልብስ ምን አይነት ቀለም አለው?
- የአባታችሁ ፣የእናታችሁ የልብስ ቀለም ምን አይነት ነው?




ምስል .3.20

ሱሪና ሹራባችሁ የናንተስ ምን አይነት ቀለም ነው ?እስቲ ከታች ያለውን ሱሪ እና ሹራብ በሌላ ወረቀት ላይ በራሳችሁ ልብስ አይነት ቀለም ቀቡ፡፡



ምስል .3.21

የለበሳችሁትን የቀሚስ ቀለም አይነት በመቀባት ተለማመዱ ፡፡



ምስል 3.22

## ሰንደቅ ዓላማ




ምስል.3.23

## የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰንደቅ ዓላማ

ተማሪዎች የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለማት ምን ምን ናቸው?

ከታች በተሰጠው የባንዲራ ምስል መሰረት በሌላ ወረቀት ቀለማቱን ፡፡



ምስል .3.24

## የባህል አልባሳት ቀለም



ምስል 3.25



ምስል.3.26

## ባህላዊ የሴቶች ቀሚስ ቀለማት



ምስል.3.27. የባህል ቀሚስ ቀለም



ምስል .3.28 የሃመር ወጣት ሴት

- ምን ምን አይነት ቀለም ከልብሷ ላይ አያችሁ?

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. የባህልአለባሳት የአንድን አካባቢ ባህል መግለጽ ይችላሉ፡፡
2. በሀገራችን የተለያዩ የውዝዋዜዎች አይነቶች አሉ፡፡
3. ተረቶች መልካም ስነምግባርን ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡
4. የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አንድ አይነት ቀለም ብቻ ነው ያለው፡፡

# ምዕራፍ አራት
# ባህላዊ ክንዋኔዎችን ማድነቅ

ሀገራችን ላይ ብዙ ድንቀ ባህሎት አሉ ። የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የአጨፋፈር፣ የቋንቋ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ባህሎች አሉ።

- ልጆች በአካባቢያችሁ ሰርግ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
- አይታችሁ የምታውቁ ከሆነ ከሰርጉ ላይ ምን ምን አያችሁ ?
- ሽማግሌዎች የተባሉትን ሰዎች ሲያስታርቁ አይታችኋል ?

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የተለያዩ ባህሎችን መልካም ባህሎችን ትገነዘባላችሁ።
- ባህላዊ ተግባራት ፣ ውዝዋዜን እንዲሁም ሙዚቃን ታውቃላችሁ።
- ባህላዊ የሆኑ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ።
- በምስሎች የተለያዩ ባህሎችን የቤት አሰራር ፣አልባሳት፣ ጌጣጌጦችን መለየት ትችላላችሁ።

## 4.1.ባህልን የሚገልጹ መዝሙሮቸ ፣ውዝዋዜዎች ፣ሚና መጫዎት እና ምስል

### 4.1.1. ስለ ባህል የሚናገሩ መዝሙሮች

እኛ ኢትዮጵያን ከሌላው አለም የተለየ የራሳችን የሆነ ባህል እንዳለን አይታችኋል፡፡ከዚህም ውስጥ የራሳችን የሙዚቃ ቅኝት እና የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጥቀስ ይቻላል ፡፡


**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ** :- የተለያዩ ባህልን የሚያወድሱ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡ እንዲሁም የተለያዩ የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎችን ታውቃላችሁ፡፡

- ስለምታውቁት የባህል የሙዚቃ መሳሪያ ለመምህራችሁ ተናገሩ ?

የሙዚቃ መሳሪያዎቹን በምስል ተመልከቱ ፡፡



ምስል.4.1- ከበሮ



ምስል.4.2. .ክራር



ምስል .4.3.ማሲንቆ



ምስል.4.4. በገና



ምስል.4.5. ዋሽንት



ምስል.4.5. ፊላ

**እኛም አለን ሙዚቃ**

እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ

እኛም አለን ሙዚቃ ስሜት የሚያነቃ

ከበሮችን

ቡም ቡም ቡም ቡም

ክራራችን

ታታታታ

ማሲንቋችን

ላላ ላላ

በገናችን

ቦም ቦም ቦም ቦም

### 4.1.1.ሚና መጫዎት

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ** :- በአካባቢያችሁ ያሉ ባህሎችን በሚና መጫወት ትረዳላችሁ፡፡

እስቲ ከዚህ በፊት ያያችሁትን ሚና መጫዎት ተናገሩ ?

# የጋሞ አባቶች የእርቅ ስርዓት



ምስል .4.6

የጋሞ ሽማግሌዎች  በሃገር ሰላም እንዲፈጠር በማድረግ ይታወቃሉ፡፡

ተማሪዎች በቡድን በመሆን መምህራችሁ በሚሰጣችሁ የሚና ጨዋታ መሰረት ትተውናላችሁ፡፡

ሰርጎችን ፣ባህላዊ ሽምግልናዎችን እንዲሁም የተለያዩ የሃገራችን ባህሎችን አስመስላችሁ በቡድን ተጫወቱ፡፡

## የኮንሶ የእርከን ስራ

ልጆች በሃገራችን ብዙ ሚደነቁ ባህሎች አሉ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የስራ ባህል ነው፡፡

በኮንሶ ተራራማ አካባቢ አፈር በውሃ እንዳይታጠብ የእርከን ስራ ይሰራል፡፡

የእርከን ስራ እንዴት እንደሚሰራ ከመምህራችሁ በማየት የእርክን ስራን አስመስላችሁ በህብረት ስሩ፡፡

## የተለያዩ ባለሙያዎችን መስሎ መጫወት



ምስል.4.7.ሀኪም



ምስል 4.8

ልጅቷ እንደ ትራፊክ ሆና ስትጫወት፡፡

ትራፊኮች መኪኖች በአግባቡ እንዲተላለፉ ሲያደርጉ ይሄን አይነት ምልክት ያሳያሉ፡፡

### 4.1.3. ባህሎችን የሚያሳዩ ምስሎች፡

*መግቢያ*

በተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች እንደባህላቸው የተለያዩ ማጌጫዎች አሉአቸው ፡፡

ባህልላዊ እሴቶች በተለያየ መንገድ ይገለጻሉ፡፡ የአንድ ማህበረሰብ አኗኗር እንዲሁም ሁኔታ ከሚያዘጋጃቸው የባህል ጥበባዊው ጨቶች መረዳት እንችላለን፡፡

በእጅ የሚሰሩ የሸክላ ውጤቶች፣ የሽመናስራዎች ብሎም የቤት አሰራሮች እንዲሁም ጭፈራዎች የአንድን ህዝብ ባህል፣አኗኗር እና ሁኔታ ይገልጻሉ፡፡

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ :-** የተለያዩ ባህሎችን የሚያሳዩ ውብ ምስሎችን ታያላችሁ ስለባህሎችም ታውቃላችሁ፡፡

- የሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን ምስልላይ ያያችሁትን ለመምህራችሁ ተናገሩ?ጭፈራዎቹስ ምን ያመሳስላቸዋል?



ምስል.4.9 የኮንሶ ማህበረሰብ ጭፈራ



ምስል.4.10 የሀመር ኢቫንጋዲ ጭፈራ



ምስል 4.11 የዳሰነች ማህበረሰብ ጭፈራ



ምስል 4.12 የኛንጋቶም ማህበረሰብ ጭፈራ

## ባህላዊ መዋቢያዎች



ምስል.4.13



ምስል.4.14



ምስል.4.15

## ባህላዊ የቤት አሰራሮች

በሃገራችን የተለያዩ ባህላዊ የቤት አሰራሮች ይገኛሉ። በደንጋይ ፣ በጭቃ፣ በሳር ፣ በቀርክሃ ቤቶች ይሰራሉ። በሀገራችን የባህላዊ ቤት አሰራር ብዙ ጊዜ ጣራቸው የሳር ክዳን የሆኑ ጎጆ ቤቶች ናቸው ።



ምስል.4.16 የጉራጌ ማህበረሰብ ቤት አሰራር



ምስል.4.17.የጋሞ ማህበረሰብ ቤት አሰራር



ምስል 4.18. የደቡብ ኦሞ አካባቢቤት አሰራር

- በአካባቢያችሁ ቤቶች በምንድን ነው የሚሰሩት ?

## ባህላዊ የቡና አቀራረብ ስርዓት



ምስል.4.19

## ባህላዊ  የጥበብ ስራዎች



ምስል.4.20. በእጅ የሚሰራ ባህዊ ሰፌድ

## ባህላዊ ሸመና እና ፈትል



ምስል.4.21 ጥጥ የምትፈትል ሴት



ምስል.4.22 ሸመና የሚሰራ ሰው

# በባህላዊ ሽመና የተሰሩ ባህላዊ ጨርቆች



ምስል.4.23



ምስል.4.24.ባህላዊ የሀበሻ ቀሚስ

## 4.2..አካላዊ እንቅስቃሴ

የሰውነት እንቅስቃሴ የምንለው በቀላል የሙዚቃ ምቶች ልጆች ሰውነታቸውን የሚያንቀሳቅሱበት ድርጊት ነው፡፡ ልጆች እንደ ውዝዋዜ ያለ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ከምት ጋር በማዛመድ በነጻነት የሚንቀሳቀሱበት ተግባር ነው፡፡

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ :-** ስለ ቀላል የሰውነት እንቅስቃሴዎች ታውቃላችሁ እንዲሁም ቀላል የሰውነት እንቅስቃሴዎችን መተግበር ትችላላችሁ፡፡

- እስቲ ተማሪዎች የምታውቁትን አንድ ቀላል የእግር እንቅስቃሴ ወይም ጨዋታ ለመምህራችሁ አሳዩ ?



4.2.1 .ልጁ የሰውነት እንቅስቃሴ ሲያደርግ



## 4.2 ልጁ እየዘለለ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. በባህላችን የተጣሉ ሰዎችን ማስታረቅ ተገቢ ተግባር ነው፡፡
2. ሃገራችን ውስጥ ብዙ የሚደነቁ ባህሎች አሉ፡፡
3. በሃገራችን አልባሳት አንድ አይነት ብቻ ናቸው፡፡
4. በሃገራችን የተለያየ የሰርግ ስርዐቶች አሉ፡፡
5. በሃገራችን የተለያዩ የቤት አሰራሮች የሉም፡፡
6. በእጅ የሚሰሩ አልባሳት እንዲሁም የተለያዩ የእደ ጥበብ ውጤቶች የአንድን ህዝብ ባህል እና አኗኗር ይገልጻሉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# ጥበባዊ ትግበራ ማቅረብ

ጥበባዊ ትግበራ በተለያዩ መንገድ ተማሪዎቹን አሳታፊ በማድረግ የሙዚቃን ፣የስዕልን ፣ የትወናን ጥበብ በአንድ የምንተገብርበት መንገድ ነው ።

በዚህ ምዕራፍ በተግባር የተደገፉ መዝሙሮች፣ስዕሎችን እንዲሁም ውዝዋዜዎችን በማቀናጀት እንማራለን፡፡

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- በመዝሙር ፣በውዝዋዜ በመታጀብ ስለ ቀለም ታውቃላችሁ፡፡
- በቡድን ቀለል ያሉ መዝሙሮችን ትዘምራላችሁ፡፡
- አካባቢያቸውላይ ያሉ የተፈጥሮ ቀለሞች መግለጽ ትችላላችሁ፡፡
- ቀለል ያሉ መዝሙር እና ውዝዋዜን በአንድ ላይ ታቀርባላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሃብቶችን የተመለከቱ መዝሙሮች ትዘምራላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሃብቶችን በስዕል እና በፎቶ ታውቃላችሁ፡፡

## 5.1. የህብረት ጨዋታዎች

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ :- ቀለማን የሚናገሩ ጨዋታዎችን ታውቃላችሁ፡፡**

እስቲ አንድ የምትወዱትን ጨዋታ ተጫውታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ?

### የቀለም የቡድን ጨዋታ

ልጆች ሶስት ወይም አራት በመሆን ትጫወታላችሁ፡፡ አንድ ልጅ ጨዋታውን እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ጨዋታውን የሚመራ ልጅ ጨዋታውን አረንጓዴ፣አረንጓዴ እያለ ይዘምራል፡፡

የሚጫወቱት ልጆች አረንጓዴ ሲባል ባሉበት ዱብ ዱብ ይላሉ፡፡ድንገት ቢጫ ሲል ይቀመጣሉ፡፡ቀይ ሲል ቀጥ ብለው ይቆማሉ፡፡ የጫዋታውን መሪ ልጅ በመከተል ይተገብራሉ፡፡ያልታዘዘውን ያደረገ ልጅ ጨዋታውን ይፎርሻል፡፡ለምሳሌ ቀይ ሲባል የተቀመጠ ወይም ዱብ ዱብ ያለ በጨዋታው ይፎርሻል፡፡

**ቀለሟን የነካ**

**አጨዋወት**

በጨዋታው በግል ወይም እስከ አምስት ልጆችን በቡድን መምረጥ ፡፡መምህሩ የአንድ ቀለም ስም ሲጠራ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኝን መምህሩ የጠራው ቀለም አይነት የያዘ ቁስ በቶሎ በመንካት ታሳያላችሁ ፡፡ ቶሎ ቀለሙን የነካ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

## 5.2. በህብረት መዘመር

**ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ** :- ስለ ቀለም የሚያነሱ መዝሙሮችን ከእንቅስቃሴ ጋር በማጀብ ትዘምራላችሁ፡፡

የምታውቁትን መዝሙር ለመምህራችሁ ዘምሩ ?

ልጆች ከታች ያለውን መዝሙር መምህራችሁ በሚሰጣችሁ ዜማ ዘምሩት፡፡መዝሙሩ በቡድን ሆናችሁ የምትዘምሩት ነው፡፡

## ማን ነው ቀይ ያደረገው

ማን ነው ቀይ ያደረገው
እኔ ነኝ ቀይ ያደረግኩት
ምን ነው ቢጫ ያደረገው
እኔ ነኝ ቢጫ ያደረግኩት
ምን ነው ነጭ ያደረገው
እኔ ነኝ ነጭ ያደረግኩት
ምን ነው ጥቁር ያደረገው
እኔ ነኝ ጥቁር ያደረግኩት

## 5.3. ስለ ተፈጥሮ ሃብት እና በዙሪያችን ስላሉ የተፈጥሮ ቀለሞች

በዙሪያችንያሉ ነገሮችን ተመልከቱ ዛፎችን፣ አበቦችን፣ ተራሮችን፣ እንስሶችን ፣ ወንዞችን የራሳቸው ቀለም አላቸው።

ቀለሞችን ለመቀባት ብንፈልግም ቀለሞቸን ከአካባቢያችን ካሉ ነገሮችን እናገኛለን አረንጓዴ ብትፈልጉ ከተለያዩ ቅጠሎች ታገኛላችሁ።ቀይ ብትፈልጉ ከቀይ አፈር ከአበቦች ማግኘት ይቻላል።

**ይሄንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ :-** በሚና መጫዎት የተለያዩ እንስሳትን ድምጽ ታስመስላላችሁ እንዲሁም ቀለማቸውን ታውቃላችሁ፡፡

- እስቲ በሬዎች እንዴት እንደሚራመዱ እንዲሁም እንዴት እንደሚጮሁ ተናገሩ ?
- ተማሪዎች ጥቁር ቀለምን ከምን ማዘጋጀት እንችላለን እስቲ የምታውቁትን ተናገሩ?



ምስል.5.1 በተፈጥሮ የተዋበው የአባይ ወንዝ

የዛፉን ቀለም ፣የወንዙን ቀለም እና የሳሩን ቀለም ተመልከታችሁ ያያችሁትን ቀለም ተናገሩ ።



ምስል.5.2. የእንሰት ተክል

የእንሰት ተክሎችስ ቅጠላቸውና ግንዳቸው ምን አይነት ቀለም አለው ?



ምስል.5.3 ተራራ አካባቢ የተሰራች ጎጆ

# መዝሙር

## ሃገሬን ጎብኘቼ

:

ተራሮችን አቋርጬ

እርሻ ማሳ ተመልክቼ

ከምንጮቹም ተጎንጭቼ

ሃይቆቹንም አይቼ

ኮ ር ቻ ለ ሁ

ሃ ገ ሬ ን

አ ይ ቼ



ምስል.5.4 ጫሞ ሃይቅ

## የወፎች ቀለም

ወፎች ሲዘምሩ ሰምታችኋል በጣም የሚያምር ድምጽ አላቸው ::

ድምጻቸው ብቻ ሳይሆን የሚያምሩ የተለያዩ ቀለም ያሏቸው ላባዎችም አሏቸው።



ምስል 5.5 የተለያየ ቀለማት ያላቸው ወፎች



ምስል 5.6.አረንጓዴ ፣ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለው በቀቀን ወፍ



ምስል.5.7.ሰማያዊ ቀለም ያላት ወፍ




ምስል.5.8

ሰማያዊ ፣አረንጓዴ፣ቀይ እና ቡርትካናማ ቀለም ያላቸው ወፎች

ልጆች በአካባቢያችሁ ያሉ ወፎች ምን አይነት ቀለም አላቸው?

የወፏን ቀለም ማቅለም ፡፡



ምስል.5.9



ምስል 5.10.ፒኮክ

ፒኮክ በተለያየ ቀለም ያሸበረቀ ላባ አላት፡፡

## በአካባቢያችሁ ያሉ አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች ቀለም



ምስል.5.11.ብርቱካን



ምስል.5.12.ካሮት



ምስል.5.13.ማንጎ



ምስል.5.14.ሙዝ




ምስል.5.15.አቮካዶ



ምስል5.16. ቲማቲም


ተማሪዎች የአቦካዶ ቀለም ምን አይነት ነው? የቲማቲምስ?

ከዚህ በታች የተሰጧችሁን ምስሎች በትክክለኛው ቀለም በሌላ ወረቀት ላይ አቅልሙ




ምስል.5.17

ይሄ የማንጎ ዛፍ ነው ቅጠሎቹ ምን ቀለም መሆን አለባቸው?




ምስል.5.18.

ይሄስ ምንድን ነው ቀለሙስ ምን መሆን አለበት



ምስል.5.19

ይሄስ ምንድን ነው ቀለሙስ ምን መሆን አለበት



ምስል.5.20

ይሄ ምን አትክልት ነው ቀለሙስ ምን መሆን አለበት?

# እንሰሳት እና ቀለማቸው



ምስል.5.21



ምስል.5.22

የሜዳ አህዮችን ከተመለከታችሁ ደሞ የቆዳቸው ቀለም ላይ ነጭ እና ጥቁር ቀለም በመስመር ሆኖ ታያላችሁ።

## የተፈጥሮ ሀብቶች

## ወንዞች፣ ሃይቆች እንዲሁም ደኖች የተፈጥሮ ሃብት ከምንላቸው ውስጥ ይመደባሉ ፡፡



ምስል.5.23. ኦሞ ወንዝ

### የቃል መልመጃ

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1. በአካባቢያችሁ ካሉ የተፈጥሮ ቀለማት የምትወዱት ቀለም ምንድን ነው?
2. በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ በብዛት ያሉት ቀለሞች ምንምን ናቸው ?
3. ስለ አካባቢያችሁ የሚናገር አንድ መዝሙር ዘምሩ?

# የእይታና የትወና ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## አንደኛ ክፍል

የ ደቡብ ብሔሮች ብረሰቦች ሕዝቦች ክልል መንግስት
ትምህርት ቢሮ